የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፹
አዲስ አበባ መስከረም ፳፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Fourth Year No.80
ADDIS ABABA October 7, 2016

**ማውጫ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ደንብ.............................ገፅ ፩

**CONTENT**

The Addis Ababa City Government Job Creation and Food Security Agency Regulation ......................Page 1

## ደንብ ቁጥር ፹/፪ሺ፱

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ ደንብ

በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዘርፍ ለዜጎች ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር የከተማችንን ነዋሪ የኑሮ ደረጃ ማሻሻል እና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች መፋጠን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ በመቅረፅ ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

## Regulation No. 80/2016

## A Regulation to Provide the Establishment of the Addis Ababa City Government Job Creation and Food Security Agency

**Whereas** , it is found necessary to design and implement the strategy for small and micro enterprises development in order to create broad job opportunities for citizens in the small and micro enterprises development sector so as to accelerate the social and economic development and improve the life standard of the residents of the city;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በዘርፉ በርካታ የሥራ እድል መፍጠር የተቻለ ቢሆንም በከተማችን የነዋሪውን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችል ፖሊሲና ስትራቴጂ ከዚህ በፊት ያልነበረ በመሆኑ በተለያዩ አካላት ሲከናወኑ የነበሩ የምግብ ዋስትና ስራዎች ወጥነትና ቅንጅት የጎደላቸዉ በመሆኑ በርካታ የከተማችን ነዋሪዎች ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ እየሆኑ በመምጣታቸው፤

Whereas, as many of the residents of our city has become vulnerable to social and economic and economic problems due to the absence of policy and strategy that ensures the food security of the residents of the city and the lack of sustainability and coordination among the various organs that carry out the food security activities even if a lot of job opportunities has been created in the sector;

የከተማችን የምግብ ዋስትና ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም የሚደነግግ ህግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

Whereas, it has been found necessary to issue a regulation to establish the job creation and food security agency so as to solve the food security problems of our city in a sustainable manner;

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩/ረ/ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ አንቀጽ ፹፬ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**Now**, **therefore**, in accordance with article 23(1)(f) of the Addis Ababa city government revised charter proclamation number 361/2003, and article 84 of the Addis Ababa city government executive and municipal service organs re-establishment proclamation number 35/2012, the Addis Ababa city government cabinet has issued this regulation as follow.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ደንብ ቁጥር ፹/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## Part One
## General Provisions

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "Regulation to Provide the Establishment of the Job Creation and Food Security Agency Regulation number 80/2016."

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት አዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ቢሮ"** ማለት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ነው፤

፬. **"ኤጀንሲ"** ማለት የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፤

፭. **"የምግብ ዋስትና"** ማለት እያንዳንዱ ዜጋ መጠንና ጥራትን በአማከለ መልኩ በዘላቂነት እና ባልተቋራረጠ ሁኔታ ምግብ በማግኘት የነፍስ ወከፍ የዕለት ፍጆታን ፪ሺ፪፻ ካሎሪ እንዲደርስ በማድረግ ጤናማና አምራች እንዲሆን ማድረግ ነው፤

፮. **"ልማታዊ ሴፍቲኔት"** ማለት ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ግለሰቦችና ቤተሰቦች ከልማት ስራ እና ከዘላቂ ሀብት ፈጠራ ስራዎች ጋር በማስተሳሰር የገቢ ምንጭ የማስገኛ አማራጮችን በማስፋትና ምርታማ እንዲሆኑ በማብቃት የራሳቸውን ጥሪት ገንብተው የምግብ ዋስትናቸውን በዘላቂነት እንዲያረጋግጡ ማስቻል ነው፤

፯. **“ሥራ ዕድል”** ማለት የመሥራት አቅም እያላቸው በተለያየ ምክንያት ወደ ሥራ ያልገቡ ነዋሪዎች በማህበረሰብ አቀፍ ስራዎችና በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ገቢ የሚያገኙበት የድጋፍ ዓይነት ነው፤

## 2. Definition

In this regulation, unless the context otherwise requires:

1. “**City**” means the Addis Ababa city;
2. “**Government**” means the Addis Ababa city government;
3. “**Bureau**” means the micro and small scale enterprises development bureau;
4. “**Agency**” means the job creation and food security agency;
5. “**Food Security**” means the provision of quality and enough food in a sustainable and continuous way to meet the daily 2,200 calorie intake of an individual so as to have a healthy and productive citizen;
6. “**Developmental Safety Net**” means enabling those individuals and families, who have perilous food security problem, to ensure their food security in a sustainable manner by creating their own wealth through linking them with developmental activities and continuous wealth creation activities, expanding their income generating opportunities and capacitating them to become productive;
7. “**Job Opportunity**” means a type of support in which residents, who can earn but unable to do so due to various reasons, engage in community wide works and sustainable life improvement sub-programs and obtain an income;

፰. **“የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ”** ማለት የአካባቢው አስተዳደርና በህብረተሰቡ የሚታቀዱ የአረንጓዴ ልማት፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የወንዞች ዳርቻ ልማት፣ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት እና የመሳሰሉት ስራዎችን በመስራት የዕለት ገቢ ለማግኘት የሚያስችል የድጋፍ ዓይነት ነው፤

፱. **“የኑሮ ማሻሻያ”** ማለት በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ በራሳቸው ጥረት አኗኗራቸውን ለማሻሻል የሚደረግ ጥረትን የሚያካትት የድጋፍ ዓይነት ነው፤

፲. **"ሽግግር"** ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ወይም ማህበረሰብ ከማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች ወደ ኑሮ ማሻሻያ ከኑሮ ማሻሻያ ወደ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የሚሸጋገርበት ሂደት ነው፤

፲፩.**“ምርቃት“** ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ወይም ማህበረሰብ ከማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎችና ከዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑሳን ፕሮግራም ተጠቃሚነት መውጣትን የሚያመለክት ሂደት ነው፤

፲፪.**"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፫.በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያጠቃልላል፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ውስጥ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

8. “**Community Wide Development Works**” means a type of support that enables to generating a daily income through engaging in the works of green development, dry waste detainment and removal, riversides development, coordinated stream development and such others which are planned by the community and the local administration;
9. “**Life Improvement**” means a type of support that includes the self-endeavor of those individuals who are living under low life condition so as to improve their lives;
10. “**Transition**” means the process transferring of an individual or a family or community from community wide to life improvement from life improvement to micro enterprises;
11. “**Graduation**” means a process that indicates the leaving of an individual or a family or community from the community wide development works and the sustainable life improvement sub-program benefits;
12. “**Person**” means any natural or juridical person;
13. Any expressions in the masculine gender shall be applicable to the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This regulation shall be applicable in the Addis Ababa city government.

## ክፍል ሁለት

## ዓላማ፣መቋቋም እና ሥልጣንና ተግባር

### ፬. ዓላማ

በከተማችን ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉ እና የመስራት አቅም ያላቸው እንዲሁም ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎች በማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎችና በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች አማካኝነት የስራ እድል በማመቻቸትና ገቢያቸውን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ከድህነት እንዲወጡ ማድረግ ነው፡፡

### ፭. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ከዚህ በኋላ "**ኤጀንሲ**" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለቢሮ ይሆናል፡፡

### ፮. አደረጃጀት

ኤጀንሲው የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. ዋና ዳይሬክተር፤

፪. ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤

፫. ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል፤

፬. ኤጀንሲው በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፤

፭. የኤጀንሲው ዋና እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር በሹመት ይመደባሉ፡፡

## Part Two

## Objective, Establishment, Power and Duties

### 4. Objective

To liberate residents, who are living below the poverty line, can't earn or those vulnerable to social problems, of our city from poverty through ensuring their food security by facilitating job opportunities using community wide development works and sustainable life implement sub-programs and increasing their income.

### 5. Establishment

1. The Addis Ababa city government job creation and food security agency (hereinafter the "**Agency**") is hereby established as an autonomous organ having its own legal personality.
2. The agency shall be accountable to the bureau.

### 6. Organization

The agency shall the following organization:

1. General Director;
2. Deputy general director;
3. Other necessary departments and staffs;
4. The agency shall have offices at sub-city and woreda level;
5. The general director and deputy general director of the agency shall be assigned through appointment.

## ፯. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

፩. የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎችና የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑሳን ፕሮግራሞች አሰራሮችን ይነድፋል፣ መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባር ላይ ያውላል፤

፪. በማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎችና በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም የተጠቃሚዎች ልየታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ግልጽነትና ተጠያቂነት ባሰፈነ መልኩ ህብረተሰቡን በማሳተፍ እንዲከናወን ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል ፤ ያረጋግጣል፤ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፫. መስራት እየቻሉ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት ሥራ ሳይኖራቸው በከፋ ድህነት ላይ የሚኖሩትን የከተማ ነዋሪዎችን መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ይተነትናል፣ ሲፈቀድለትም በማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎችና በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፬. በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተለዩ ነዋሪዎችን ከማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ወደ ዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ እና ወደ እድገት ተኮር ዘርፍ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፤

፭. በፕሮግራሙ የታቀፉ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተጠቃሚነታቸው ጊዜ ሲያበቃ የማስመረቅ ስራ ይሰራል፤

፮. በማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች እና በኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ለሚታቀፉ ተጠቃሚዎች እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን ለማከናወን እንዲያስችል ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ይዘረጋል፤ መረጃዎችን ያደራጃል ፤ ይተነትናል ፤ያሰራጫል ፤ጥበቃ ያደርጋል፤

## 7. Power and Duties of the Agency

1. Design procedures of community wide development works and sustainable life improvement sub-programs so as to ensure food security; prepare programs; implement the thereof upon approval;
2. Carry out the identification of beneficiaries of community wide development works and sustainable life improvement sub-programs together with the concerned stakeholders in a transparent and accountable manner though participating the community; follow-up, support and ensure the thereof; and cause remedial measures are to be taken;
3. Collect, organize and analyze information about the city residents that can earn but unable to do so due to social and economic problems and live under extreme poverty; cause them to be beneficiaries of community wide development works and sustainable life improvement sub-program upon its approval;
4. Transfer residents that were identified to be beneficiaries of the food security program from community wide development works to sustainable life improvement and development centered sectors;
5. Support and follow-up individuals and families included in the program; carry out their graduation when their period of time as a beneficiary is over;
6. Establish a modern information system about beneficiaries included in the community wide development works and life improvement programs and to carry out other related activities; organize, analyze, distribute and protect the information;

፯. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያሉ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር ግንኙነት በመመስረት የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፤
፰. አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በአጋርነት ለመስራት የሚያስችሉ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤
፱. ለኤጀንሲው የተመደበውን በጀት በወቅቱ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በተያዘው እቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
፲. የኤጀንሲውን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቢሮው፤ ለካውንስሉ ፣ ለፌደራል የከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ እና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤
፲፩. የኤጀንሲውን ሂሳብ መግለጫዎች እያዘጋጀ በሩብ፣ በግማሽና በዓመቱ ማጠቃለያ እና እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ ለቢሮው ፣ ለካውንስሉ እና ለፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሪፖርት ያቀርባል፤
፲፪. ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ፣ይከሰሳል፤
፲፫. የኤጀንሲውን ዓላማዎች ለማሳካት በቢሮው ወይም በካውንስሉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፰. <u>የካውንስሉ መቋቋም</u>

፩. የምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ካውንስል ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጣ ሆኖ በማዕከል፣ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤
፪. የካውንስሉ አደረጃጀት ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል፤
፫. የካውንስሉ ሰብሳቢ የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ይሆናል፤
፬. የኤጀንሲው ዋና ዳሬክተር የካውንስሉ ፀሐፊና አባል ይሆናል፡፡

7. Share experience with local and foreign institutions that have similar objective through establishing a relation;
8. Design and implement systems that enable to work in alliance with relevant institutions;
9. Follow-up and control that the allocated budget for the agency is deposited at the appropriate time; effect payments in accordance with the approved plan;
10. Prepare the performance and financial report of the agency and submit it to the bureau, council, the federal job creation and food security agency of cities and the concerned bodies;
11. Prepare the account statements of the agency and submit a quarterly, half year and annual reports and also at any time as necessary to the bureau, council and the federal job creation and food security agency of cities;
12. Enter into contracts; sue and be sued;
13. Carry out other activities delegated by the bureau or council for the attainment of objectives of the agency.

## 8. <u>Establishment of the Council</u>

1. The food security and development safety net program council is hereby established under this regulation, being constituted from various institutions, at central, sub-city and woreda level.
2. The particulars about the organization of the council shall be specified through a directive.
3. The chairperson of the council shall be the mayor of the city government.
4. The general director of the agency shall be the secretary and the member of the council.

## ፱. የካውንስሉ ሥልጣንና ተግባር

ካውንስሉ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የኤጀንሲውን ስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅዶችን ይገመግማል፣ አስተያየት ይሰጣል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

፪. የተጠቃሚዎች ልየታ ፍታሃዊ በሆነ መንገድ መከናወኑን ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

፫. ካውንስሉ ለሚያከናውናቸው ተግባራት እንዲረዳው የፌደራል፣ የክልሎች እና የሌሎች ሀገራትን አደረጃጀት፣ አፈጻጸምና መሰል ተሞክሮዎችን የሚያጠና ኮሚቴ ወይም ግብረ ኃይል ሊሰይም ይችላል፤

፬. የከተማውን የምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ቅንጅታዊ አሰራር በበላይነት ይመራል ፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

፭. ባለድርሻ አካላት ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚያቀርቡትን ዕቅድ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

፮. ኤጀንሲው የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ምክር፣ ድጋፍና አመራር ይሰጣል፤

፯. የምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም አጠቃላይ አፈጻጸም ይከታተላል ፣ ይደግፋል፤

፰. የምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ጠቅላላ የተጠቃሚዎችን ቁጥር ይወስናል፣ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

## 9. Power and Duties of the Council

The council shall have the following power and duties:

1. appraise the strategic and annual plan of the council; give opinions; set direction;
2. evaluate that the identification of beneficiaries was being carried out fairly; set direction;
3. may assign a committee or task force to study the organization, performance and such other experiences of similar institutions of the federal, regional and other countries so as to assist the activities carried out by the council;
4. lead, follow-up and support the collaborative performance of the food security and development safety net program of the city superiorly;
5. appraise the implementation plan of the program submitted by stakeholders; set direction;
6. provide consultation, support and leadership for attainment of the objectives of the agency;
7. follow-up and support the general performance of the food security and developmental safety net program;
8. decide the total number of the beneficiaries of the food security and developmental safety net program; ensure the implementation of the thereof;

፱. የምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰቦችና ቤተሰቦች የምግብ ዋስትናቸው ሲረጋገጥ እንዲሸጋገሩ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲. ለስራ አመራር እና ለቴክኒክ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ድጋፍ ይሰጣል፣ይከታተላል፡፡

## ፲. የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩. ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣ ኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል ይቆጣጠራል፤

፪. ኤጀንሲውን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

፫. የስራና በጀት እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬. የእቅድ አፈፃፀም ወቅታዊ ሪፖርት ለቢሮው ያቀርባል፣ ያስገመግማል፤

፭. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ለሚደረግ ግንኙነት ኤጀንሲውን ይወክላል፤

፮. የኤጀንሲውን ተልዕኮ ለማሳካ ከአጋር አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፯. ሌሎች ከቢሮው የሚሰጡትን ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

## ፲፩. የምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

9. give a decision to transfer those individuals and families that are beneficiaries of the food security and developmental safety net program when their food security is assured;
10. provide support for the management and technical coordination committees; follow-up same;

## 10. Power and Duties of the General Director

The general director, being accountable to the bureau, shall have the following power and duties:

1. Implement the power and duties given to agency; lead, coordinate and control the agency superiorly;
2. Design management systems focusing on strategic issues that makes the agency effective; follow-up the implementation of the thereof; submit a report to the concerned organs;
3. Prepare the work and budget plan; implement the thereof upon approval;
4. Submit the timely plan performance report to the bureau; cause the appraisal of the thereof;
5. Represent the agency in its dealings with the third parties;
6. Work cooperatively with alliance organs for the attainment of the mission of the agency;
7. Carry out other additional activities delegated by the bureau.

## 11. Power and Duties of the Deputy General Director

The deputy general director, being accountable to the general director, shall have the following power and duties:

፩. የኤጀንሲውን መዋቅራዊ አደረጃጀት ጥናት መሰረት በማድረግ የስራ ክፍሎችን ይመራል፣ያስተባብራል፤
፪. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
፫. የኤጀንሲውን የስራ ዕቅድ ዝግጅትና አፈጻፀም ይከታተላል ይደግፋል፤
፬. በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፪. የበጀት ምንጭ

የኤጀንሲው በጀት በአስተዳደሩ ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት የሚመደብ ይሆናል፡፡

### ፲፫. የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

፩. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤
፪. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በውስጥ ኦዲተርና በከተማው ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፤
፫. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብት፣ ገንዘብ እና የንብረት ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ የከተማው የፋይናንስ አስተዳደርን ሕጎች የተከተለ ይሆናል፡፡

### ፲፬. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

1. Lead and coordinate the departments based on the structural organization study of the agency;
2. Act on behalf of the general director in his absence;
3. Follow-up and support the preparation and performance of the work plan of the agency;
4. Carry out other activities delegated by the general director.

## Part Three
## Miscellaneous Provisions

### 12. Source of Budget

The budget of the agency shall be allocated by the government or non-governmental organs.

### 13. Keeping Books of Accounts

1. The agency shall keep complete and accurate books accounts.
2. The books of accounts and money related documents of the agency shall be inspected annually by the internal auditor and the general auditor of the city.
3. The retainment and recording of the books of accounts, money and property documents of the agency shall follow the financial administration laws the city.

### 14. Duty to Cooperate

Any person shall have the duty to cooperate for the implementation of this regulation.

፲፭. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፮. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረም፡፡

፲፯. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከመስከረም ፳፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**መስከረም ፳፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲሰ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**15. <u>Power to Issue Directive</u>**

The bureau may issue a directive that help to execute this regulation.

**16. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any regulation, directive or customary practice, which is inconsistent with this regulation, shall not be applicable on matters covered under this regulation.

**17. <u>Effective Date</u>**

This regulation shall enter in to force as of the 7th day of October 2016.

**Done at Addis Ababa**

**This 7th day of October 2016**

**Diriba Kuma**

**Mayor of Addis Ababa City**